# አማራን ስለማይወክል “ሕገ-መንግስቱ አይደለም” – ዶ/ር ደሳለኝ ጫኔ

May 1, 2020

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አገራችንን ከገባችበት ቅርቃር ለማውጣት የምንከተላቸው አማራጮች ሕገ መንግሥታዊ አማራጮችን ብቻ ነው፣ ሌላው መንገድ አይታሰብም ብለዋል። በድጋሚ የአማራ ሕዝብና መላው ኢትዮጵያዊያን ያልተሳተፉበትን የትህነግ/ኦነግ የጫካ ሰነድ ልክ ቅቡልነት እንዳለው አገራዊ ሰነድ አድርገው ለማቅረብ ሞክረዋል።




ስለዚህ የአማራ ሕዝብ ለ25 ዓመት በትዕግስት ያቀረበው በህገ መንግስቱ ውስጥ ፍላጎቴ፣ መብቴና ጥቅሜ ይካተትልኝ የሚለው ህጋዊና ፍትሃዊ ጥያቄው በመንግስት በተደጋጋሚ ተቀባይነት ካላገኘና ውድቅ የሚደረግ ከሆነ፣ በዚህ ህገ መንግስት ላይ ተከታታይ የተቃውሞ ዘመቻ ከመጀመር ውጭ ሌላ አማራጭ አይኖረንም ማለት ነው።

ስለዚህም:-

1) በመጀመሪያ ለቀጣይ አንድ ሳምንት የሚቆይ ተከታታይ የማህበራዊ ሚዲያ ዘመቻ መክፈት። የዘመቻው መሪ ቃልም “ሕገ-መንግስቱ አይደለም”/ “Not My Constitution”, #NotMyConstitution በሚል መሪ ቃል ወጥነትና ተከታታይነት ያለው ዘመቻና ተቃውሞ በፌስቡክ በአማርኛ፣ በትዊተር በእንግሊዘኛ

ማካሄድ። በዩቲውብና በፌስቡክም የ30 ስከንድ ቪዲዩ በማዘጋጀት የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አማራውን እንደማይወክለውና እንደማንቀበለው የሚገልጽ የአማርኛ/እንግሊዝኛና ሌሎች ቋንቋዎች መልዕክት ማስተላለፍ እንቀጥላለን።

2) በቀጣይ በምንስማማበት ቀን ጀምሮ ደግሞ መላው የአማራ ህዝብ በሚኖርበት አካባቢ ህገ መንግስቱ እንዲሻሻል ፔቲሽን የማሰባሰብና፣ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የማስገባት ስራ መስራት፣

3) በተራ ቁጥር አንድና ሁለት የተካተቱትን ሂደቶች ሞክረን መንግስት ለአማራ ህዝብ ጥያቄዎች ጆሮ የማይሰጥ ከሆነ፣ በቀጣይ የህገ መንግስቱን ቅጅዎች እያሰባሰቡ በአደባባይ የመቅደድ፣ የአማራ ተማሪዎች የክልልና ብሔራዊ መዝሙሮች ሲዘመሩ የመጮህና ተቃውሞ የማሰማት፣

4) እንዲሁም እነዚህ ሁሉ ሰላማዊ የትግል ሂደቶች ተሞክረው በመንግስት በኩል እምቢተኝነቱ ከቀጠለ አማራው ሌሎችም ሰላማዊና በየደርጃው የሚደረጉ የተቃውሞ ርምጃዎችን ወደመቀጠል ይሸጋገራል።

አጀንዳ ሳንደራርብ ወደስራ!
ሕገ መንግስቴ አይደለም!
ህገ መንግስት ይስተካከል፣ ይሻሻል ወይም ይቀየር!